# ሟርተኞቹ ከእግዚአብሔርም ጋር |ይሳፈጣሉ´እንዴ?!

ዮናስ 8/1/12

|በአገራችን ባህል በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ሁሉም ነገር ቀድሞ ወደነበረበት ይመለሳል። እነሱም አንድ ሰው ሲታመም ወይም ሲታሰር ነው። በሆነ ምክንያት የሚያጋጥም እሥራት የሰው ልጅ ከተፈጥሮ የተሰጠውን የነፃነት ፀጋ መገፈፍ ማለት ነው። ከህግ አንፃር ግለሰቡ ጥፋተኛ ይሁን ወይም አይሁን ሁኔታውን አይለውጠውም። በዚህ ጊዜ የተቀየመ ይቅር ይላል፤ የሆነው ሁሉ እንዳልሆነ ይቆጠራል ማለት ነው። ሌላው ህመም ሲሆን እንደሌላው ሁሉ ሙሉ ጤነኛ የነበረ የአልጋ ቁራኛ ሲሆን፤ ቀደም ሲል የነበረ የሐሳብም ሆነ የአካል ግጭት ይረሳል። እንዲያውም ተበዳይ ወገን ህመምተኛውን ይቅርታ እስከመጠየቅ ይደርሳል።´ ሪፖርተር ሐምሌ 15/2004 ተሚገት ዓምድ

የዛሬው መጣጥፌ መነሻ ከላይ የተጠቀሰውና ከሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የተወሰደው አንቀጽ ነው። ይኸውም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህመምና በእግዚአብሔር እጅ መሆን ተከትሎ ከተሰጡት አስተያየቶችና መነጋገሪያ ከነበሩት በርካታ ጉዳዮች መካከል ከሀገሬ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና የነዚሁ አካል በሆኑት የግል ፕሬሶች በኩል ሲሰነዘሩ የነበሩት ሀሳቦች እጅጉን ከሀገራችን ባህል፣ ሞራላዊና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር የተጣረሱና የማይፈቀዱ፤ ሰቅጣጭ አስተያየቶች ነበሩና ነው።

በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታና የብዙ የእምነቱ ተከታይ ባለቤት ከሆኑት ውስጥ እሥልምናና ክርስትና ዋነኞቹ ናቸው። በእሥልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የእምነቱ ዋስትናና መሠረት በሆኑት ቁርአን እና ሀዲስ (ምንም እንኳን የእምነቱ ተከታይ ባለመሆኔ) የተገለፀውን ቃል በቃል ለማለት ባልችልም የታመመን አላህ |አፊያ´ እንዲያደርገው መፀለይና |ዱአ´ ማድረግ፤ የታሰረንም መጠየቅ ተገቢና ሥርዓት መሆኑን በተደጋጋሚም ሆነ በየአጋጣሚው እንሰማለን፤ ከጎረቤቶቻችንም የአኗኗር ዘይቤ መረዳት እንችላለን።

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድም የታመመን መጠየቅ፣ የታሰረን መጎብኘት የውዴታ ግዴታና የመጽሃፍ ቅዱስም ሆነ የቅዱሳት መጻህፍቱ ትዕዛዛቶች ናቸው። በዓለም መጨረሻ ከጌታ በስተግራ የሚቆሙት ኃጥአኑ ሁሉ "እናንተ ርጉማን ከኔ ወግዱ ለሳይጣንና ለመልዕክተኞቹ ወደተዘጋጀው እሣት..." ይባላሉ። ለምን ቢሉ ጌታ እንዲህ ይላል |ብታመም አልጠየቃችሁኝምና፣ ብታሰር አልጎበኛችሁኝምና፣ ብታረዝ አላለበሳችሁኝምና … ከኔ ወግዱ´

በርግጥም  ጠቅላይ ሚኒስትሩ ታመዋል። የታመመ ሰው ደግሞ በእግዚአብሔር እጅ ነው። እንኳንስ የሳቸውን ያህል ሀገር የሚመራ እና በርካታ ሥራዎችን የሚያከናውን ቀርቶ ማንም ሰው ከህመምና ከሞት የሚያመልጥ የለም፤ የተፈጥሮ ግዴታም በመሆኑ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በርግጥም ታመዋል ያልኩበት እና እርግጥኛ የሆንኩበት መነሻዬ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጓደኛዬ ወይም ቤተሰቤ ስለሆኑ አይደለም። በትክክል የሚመለከተውና የመንግሥት ቃል አቀባይ የሆነው መሥሪያ ቤት ይፋዊ መግለጫ በመስጠቱ ነው።

በተቃዋሚና በገሬሱ በኩል የተሰጡት ፀያፍና ሰቅጣጭ አስተያየቶች የመንግሥት ቃል አቀባይ ይፋዊ መግለጫ ከመስጠቱ በፊትና ምንም ፍንጭና ጫፍ በሌለበት ሁኔታ መሆኑ ደግሞ ይብሱኑ ቅር የሚያሰኝና በእግዚአብሄር ሥራ ጥልቅ ብሎ መግባትና ከማይችሉት ጋር "የመሳፈጥ" ዓይነት ነው የሆነብኝ።

አዲስ አድማስ ጋዜጣ ካነጋገራቸው የተቃዋሚ አመራሮች መካከል የመድረክ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ኢንጂነር ዘለቀ ገሠሠ ‛ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ህመም ዋነኛ ችግር ሁሉንም ነገር ጠቅልለው በመያዝ በራሳቸው ላይ ጫና በማሳደር ራሳቸውን ለመታመም ማዘጋጀታቸው ነው´ አሉ፡፡ የአንድነት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶክተር ኃይሉ አርአያ በፊናቸው ህመሙ በጫና ምክንያት የመጣ ሊሆን እንደሚችል በመግለጽ ‛አንድ ሰው ሁሉንም መሆን አይችልም´ ማለታቸውን አዲስ አድማስ ጋዜጣ አስነብቦናል፡፡ የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሀፊ አቶ ግርማ ሰይፉ በበኩላቸው ‛እስካሁን አለመታመማቸው ትንግርት ነው´ ማለታቸውንም እንዲሁ፡፡

ከኢሣት ቴሌቪዥን ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ የአቶ መለስን ህመም በተመለከተ በውጭ አገር እና በአገር ውስጥ የሚሰጡት አስተያየቶች መልካም ባለመሆናቸው፣ አቶ መለስ ተሽሏቸው ወደ ሥራ የሚመለሱ ከሆነ እነዚህን ሁሉ አስተያየቶች ተመልክተው የፖሊሲ ማስተካከያ ማድረግ እንደሚገባቸው እርሳቸው ወደ ሥልጣን ባይመለሱ እንኳ ኢህአዴግ የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ላለፉት 20 ዓመታት የኢህአዴግ ደጋፊዎች ለእርሳቸው ልዩ አክብሮት ይሰጡ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ነጋሶ የሥልጣን ሽኩቻ ይኖራል ሲሉም በቃለ ምልልሳቸው ላይ ገልፀዋል።

የፍትህ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጦች አስተያየት ደግሞ ከሁሉም ይለያል። በሚመለከተው የመንግሥት አካል የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህመም በተመለከተ ምንም ዓይነት መግለጫ ባልተሰጠበትና ‛በእርግጥስ ታመዋል´? የሚለው ጥያቄ  ባልተመለሰበት ሁኔታና ወቅት ያለምንም የመረጃ ምንጭ በመላ ምት ብቻ ‛ታመዋል´ ከሚለው ዘገባ ተሻግረው (ምናልባትም የህመማቸው ዓይነት የእሳቸው እና የሀኪማቸው ብቻ ሊሆን እንደሚችል በሚታወቅበት ሁኔታ) የህመማቸውን ዓይነት በመዘርዘር ሳያቆሙ ግብዓተ መሬታቸውን ፈጽመው የሹመት ሥነ ሥርዓትም አከናውነዋል።

በርግጥ ፍትህና ፍኖተ ነፃነት የዜሮ ድምሩ ስብሰብ መሸሸጊያ እና የአኩራፊዎች መጠራቀሚያ በመሆናቸው ስለዚሁ አስተሳሰባቸው ሲሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ባውቅም እነሱም ኢትዮጵያውያን ናቸውና በተለይም ስለሀገሪቱ ባህል ፣ ወግና ሥርዓት እንጨነቃለን ሲሉ ይወተውታሉና |እግዚአብሄር ይማርዎት´ ማለታቸው እንኳ ቢቀር የበሬ ወለደ መርሃቸው እስከ እግዚአብሄሩ ሥራ ድረስ መዝለቁ ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም።

በሌላ በኩል ደግሞ የሀገሬ ተቃዋሚዎች ቀደም ሲል በነበራቸው የጋራ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በክብ ጠረጴዛ ውይይት አለመስማማታቸው ብቻ ሳይሆን ዕድሜ ልክ ተፈርዶባቸው ቃሊቲ ማረፊያ ቤት በነበሩ ጊዜ እንኳ ሳይቀር እርስ በርሳቸው ሲጠላልፉ እና ሲቧቀሱ እንደነበር በማስታወስ ብቻ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህመም አስመልክቶ የሰጡትን አስተያየት የተለመደ ነው ብለን ብቻ ማለፍ ያለብን  አይመስለኝም። ምክንያቱም አስተያየት ሰጪዎቹ በእድሜያቸው የገፉና ከኢትዮጵያውያን ባህልና እምነት ጋር ከዚህ ትውልድ የበለጠ ቁርኝትና እውቀቱ ያላቸው በመሆኑ፤ በአናቱም ወደዚያኛው ዓለም እየተቃረቡ መሆናቸውን ከግምት በመክተት |አይለመዳችሁ! ስለንግግራችሁም ንስሃ ግቡ!´ ስንል ልንመክራቸውና ልንገስጻቸው  ይገባል። ከሁሉ በላይ ግን በሦስት ምክንያቶች የዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ አስተያየት አንገት የሚያስደፋ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

የመጀመሪያው ምክንያት ዶክተሩ በቅርቡና ጀርመን ሀገር በነበሩ ጊዜ እሳቸው ምንም ባላሉበት ሁኔታ የስብስባቸው አካል የሆኑ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች |ዶክተሩ ጋንግሪን ይዟቸዋል፣ እርዳታ ካላገኙ እግራቸው ሊቆረጥ ይችላል´ የሚሉና በርከት ያሉ ሚርቶችን ካስነገሩ በኋላ እርሳቸው በማያውቁት ሁኔታ የባንክ ሂሳብ ከፍተው ገንዘብ እስከማሰባሰብ መድረሳቸውን አንዘነጋም።

ዶክተሩ ምንም አመማቸው ምን? ወይ እሳቸው ወይ ፓርቲያቸው ይፋዊ መግለጫ ባልሰጡበት ሁኔታ ዶክተሩ ላይ ሚማረት ባህላችን አይደለም፤ እምነቶቻችንም አይፈቅዱም። እሳቸውም ወደ ሀገር ቤት ከተመለሱ በኋላ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ እንደተናገሩት የነበሩት ዘገባዎችና የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደቶች ሁሉ የተሳሳቱና ከእውነት የራቁ መሆናቸውን  ነው።

ምን ያህል ዶክተር ነጋሶና ባልደረቦቻቸው፤ ዶክተር ነጋሶና ልሣኖቻቸው ሁሉ የተለያዩና አሁንም በመጠላለፍ ሂደት ውስጥ እንዳሉ ከዚህ ብንገነዘብም እሳቸው ግን "ተሸሎኝ ለሀገሬ እንድበቃ ላገዛችሁኝና እግዚአብሔር ይማርህ ብላችሁ በፀሎት ለደገፋችሁኝ ሁሉ አመሰግናለሁ" ብለዋል።

አንገቴን ያስደፋኝ የዶክተር ነጋሶ አስተያየት ሁለተኛ ምክንያትም የራሳቸውን ህመምና መዳን አስመልክተው የሰጡት አስተያየት ነው። ከሁሉ በላይ ሚርቱንና ስለተሰበሰበው ገንዘብ ረስተው |እግዚአብሄር ይማርዎት´ ያላቸውን ሁሉ ያመሰገኑት ዶክተር ነጋሶ የ|የእግዚአብሄር ይማርህ´ን

ትርጉም በሚገባ የሚገነዘቡና ከሁሉ በላይ ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ እንደሚያምኑበት ያመላክተናል።

ታዲያ ምነው እሳቸው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እግዚአብሄር ይማርህን ትተው |ተሽሏቸው የሚመጡ ከሆነ´ በሚል ስልት ሞታቸውን ተመኙ?

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እኮ ቢያንስ ከሌሎቹ በተለየ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በአንድ መስመር ተሰልፈው፣ አንድ ቃል አውርተዋል። በእርግጠኝነትም በአንድ ገበታም እንደተቋደሱ መገመት ይቻላል። ታዲያ ምነው ወንድም ወንድሙን እግዚአብሄር ምህረቱን ያውርድልህ ማለት ተሳነው?

ሦስተኛው የዶክተር ነጋሶ አሳፋሪ ምክንያት ደግሞ ፖሊሲ እና የግለሰብ ህመም የሚገናኙበት ምክንያት ምን እንደሆነ ወይ እሳቸው አለመዘርዘራቸው ነው፣ ወይ እኔ አለማወቁ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ለምን ሆነ? ብዬ ስጠይቅ በኔ በኩል ምላሹ አሁንም ጥያቄ ሆኖብኛል፡፡

እየተነጋገርን ያለነው የጠቅላይ ሚኒስትራችንን ህመምና ይህንኑም ተከትሎ ከዜሮ ድምር ስብስቡ መንደር ስለሚወረወሩ ባሩዶች ነው፡፡ ስብስቡ የሥልጣን ፍላጎቱን ለማርካት ከማይመስለው ጋር የሚወዳጅ፣ ከሚመስለው ጋር የሚናቆር፣ ሁሉን ነገር በእንደአስፈላጊነቱ ትርጉም እየሰጠ ወደ ኋላ ወደ ወደ ፊት አሊያም ወደ ጎን መንታ መንገድ ላይ የሚጓዝ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ስለፖለቲካ ሥልጣን ሲባል ብቻ ከሞት ጋር ቅንጅት የፈጠረ ፓርቲና ጋዜጣ በእድሜዬ የሰማሁትና የተመለከትኩት እዚህቹ ሀገሬ ላይ ብቻ ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የቃላት ብለታና ዝልዘላም ያየሁትና የሰማሁት እዚህችው ከሚገኙ ተቃዋሚዎችና ጋዜጦች ነው፡፡ ነገርዬው የህገ መንግሥታችንን አንቀጽ 75 የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ ሀገር በሥርዓትና በህግ እንጂ በግለሰብ እንደማትመራ መስማት የማይፈልጉት ወገኖች፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ዋናውና ቁልፉ ህግና የህግ የበላይነት መሆኑን የሚመሰክሩት ተቃዋሚዎችና አንዳንድ ጋዜጦች መንገዳቸው መንታ፣ መርሃቸው ደግሞ እንደአስፈላጊነቱ በመሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህመም ተንተርሰው ሀገር እንደፈረሰች፣ እንደታመመችና እንዳበቃላት አድርገው በመመጻደቅ ላይ ናቸው፡፡ ስለሆነም ሀገራችን የምትከተለው የዴሞክሪሲያዊ ሥርዓት በህግና በህግ የበላይነት ላይ ያላትን አቋምና ተቋማት ከሁሉ በላይ ደግሞ ህገ መንግሥታዊ ቃል በመበለት ላይ ናቸው፡፡

ሲጀመር ህገ መንግሥት የመተርጎም ሥልጣን የተሰጠውና ይኸው ሥልጣኑም ህገ መንግሥታዊ ማረጋገጫ ያገኘው የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት መሆኑ ይታወቃል። ይህ ባለበት ሁኔታ ግን የህገ መንግሥቱን አንቀጽ 75 እና የጠቅላይ ሚኒስትሩን የሥልጣን ዝርዝር በመበለት ላይ ይገኛሉ፡፡

የብለታቸው መዳረሻም “በማይኖር ጊዜ” የሚለው  ለአንድ እና ለሁለት ቀን እንጂ ለሣምንታት አይደለም ሲሉ ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ያመክናሉ፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን በመርህ ደረጃ እንኳ ብንነጋገር የአንድ ቤተሰብ አባላት የበላይ የሆኑት ባልና ሚስት የየራሳቸው ተፈጥሮአዊና ህጋዊ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይታወቃል። በዚሁ መሠረት ከሁለት አንዳቸው በማይኖሩ ጊዜ ተፈጥሮአዊንም ሆነ ህጋዊውን ኃላፊነት አንዳቸው ተክተው ስለመፈፀማቸው የሚያጠራጥር አይሆንም። አንዳቸው በማይኖሩ ጊዜ ሲባል እስከመቼ የሚለው በየትኛውም ቤት ገደብ ባይቀመጥለትም በሞት እስካልተለዩ ድረስ ግን አንዳቸው የአንዳቸው ተኪና ተለዋጭ መሪ መሆናቸው የግድና ተጨባጭ ሁነትና ኑሮአችን ነው። ከዚያ ባሻገር |በማይኖር ጊዜ´ የሚለው ቃል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ያህል ነው የሚለው ተዘርዝሮ መፃፍ ነበረበት የሚሉት ወገኖች ሳያውቁ የሚሰሩት ስህተት ሳይሆን መርሃቸው በሆነው እንደአስፈላጊነቱ እየተጠቀሙ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

ምክንያቱም ህገ መንግሥት የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነና ገዥ ሰነድ እንደመሆኑ መጠን ዋናና በጥቅል የሚቀርብ መሆኑንና ዝርዝር ጉዳዩና ሌሎች ተያያዥ አጀንዳዎች በሌሎች ህጎች ውስጥ ተካተው እንደሚቀርቡ፤  የመተርጎም ሥልጣን የተሰጠው ተቋም እንዳለ ያውቁታልና ነው።

ስለሆነም ከምንም ተነስቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ |በማይኖር ጊዜ´ ማለት ለሁለት ሦስት ቀናት እያሉ ገደብ መስጠትና ሀገሪቱን መንግሥት አልባ አድርጎ ማስቀመጥ |ጥማታምነት እና ሽብር ናፋቂነት´ ነው።

በአፍሪካ ህብረት ጉባዔ ላይ አዳዲስ ሀሳቦችን በማፍለቅ፣ ከሀገራችን ባሻገርም ለአህጉሪቱ ለውጥ በከፍተኛ ትጋትና የተቆርቋሪነት ስሜት በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች የአፍሪካን ድምጽ በማሰማት የሚታወቁት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአዲስ አበባ በርካታ እንግዶች በተገኙበት በተካሄደው የህብረቱና እርሳቸው በሊቀመንበርነት በሚመሩት የኔፓድ ጉባዔ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለመሳተፋቸው፤ የሴኔጋሉ ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲከፍቱት የሚጠበቀውን የኔፓድ ስብሰባ በንግግራቸው ሲከፍቱ “ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በዚህ ጉባዔ ላይ መገኘት ያልቻሉት ባጋጠማቸው የጤና ችግር በመሆኑ ከህመማቸው አገግመው ዳግም ከእኛ ጋር ተሳታፊ እንዲሆኑ እመኛለሁ” ብለው ተናገሩ፡፡

ሐምሌ 11 ቀን 2004 ዓ.ም አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ስማቸውን ለመግለጽ ያልፈለጉ አንድ የምዕራብ ዲፕሎማትን ጠቅሶ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በብራሰልስ በሚገኝ አንድ ሆስፒታል ህይወታቸውም በአስጊ ደረጃ ላይ በሆነበት ሁኔታ በህክምና ላይ ይገኛሉ ሲል ዘገበ፡፡ ሆኖም ከዚያ ቆየት ብሎ ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሚኒስትር

በረከት ስምኦን የዲፕሎማቱ መረጃ ስህተት መሆኑን ጠቅሰው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ታመው የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በተደረገላቸው ህክምና ከህመማቸው አገግመው በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል በሚል መረጃውን እንደገና በማሻሻል አውጥቷል፡፡

የአቶ በረከትን መግለጫ ተከትሎ የሀገር ውስጥ ጋዜጦች በግድ ሞተዋል፣ መስራት አይችሉም፣ የሥልጣን ሽኩቻው ጠንክሮ ቀጥሏል ዓይነትና የቢሆን ሹመት ከመስጠት ወደ ኋላ ባይመለሱም በአንፃሩ እነ Telegraph  UK, France 24 TVchannel, BBC, Reuters, AP እና ሌሎችም አጃንስ ፍራንስ ፕሬስን በመጥቀስ ትክክለኛ ዘገባ አውጥተዋል፡፡

የሴኔጋሉ ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከህመማቸው እንዲያገግሙና ህብረቱን እንዲቀላቀሉ መልካም ምኞት ሲመኙና የሀገራችንን ባህል ሲወስዱብን፤ የውጭ ሚዲያዎችም ለእውነት የቀረበ መላምታቸውን ሳይቀር በመንግሥት መግለጫ አድሰው ሙያዊ ሥነ ምግባራቸውን ሲወጡ የእኛዎቹ ግን አሁንም ሟርታቸውን በኢሣት፣ በግንቦት 7 ድምጽ፣ በፍኖተ ነፃነትና በመሰሎቻቸው በኩል በማስተጋባት ላይ መሆናቸው በእርግጥም ያማል፡፡ ከእግዚአብሄሩም ጋር ሲሳፈጡ ደግሞ የበለጠ ያሳፍራል፡፡

የሸገር ኤፍ ኤም 102 ነጥብ 1 የሸገር ካፌ ያለፈው ሣምንት እንግዳ ለረዥም ጊዜ  በህግ ነክ ጉዳዮች ጋር በየሚዲያው ላይ በሚያቀርቡት ጥልቀት ያለው ማብራሪያቸውና በህግ አምላክ በተሰኘው የህግ ትንታኔ በሚሰጡበት ፕሮግራማቸው የምናውቃቸው የቀድሞው ብዙዎቻችን “እርስዎም ይሞክሩ” በሚለው የኢትዮጵያ ራዲዮ የጥያቄና መልስ ውድድር ላይ በሚሰጡት ማብራሪያ የምናስታውሳቸው ናቸው - “ጓድ” አብዱ፡፡

አቶ አብዱ ከሸገር ካፌ ከጋዜጠኛዋ ጋር በነበራቸው ያለፈው ሣምንት ቆይታም አጀንዳቸው ይኸው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ህመምና ህመሙን ተከትሎ የሚሰነዘሩ አስተያየቶችንና ዘገባዎችን የተመለከተ ነበር፡፡ እናም አቶ አብዱ እንዲህ አሉ÷ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የህመማቸው ዓይነትና የህክምና ሁኔታ የራሳቸውና  የሀኪማቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ጠቅላይ ሚኒስትርን መታመም፣ ታምሞ ለተወሰነ ጊዜም ይሁን ላልተወሰነ ጊዜ በአንድ ዓይነት ሁኔታ ላይ ሲሆን ማስተናገድ የሚችል እያንዳንዳችን ሆደ ሰፊነት አለን ወይ? ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱም ይህን ያደርጋል ወይ? አንድ መንግሥታዊ ሥርዓት እሳቸው ታመሙ ተብሎ ሽኩቻ መኖር አለበት ተብሎስ መወራት ይገባዋል ወይ? ሽብር ለምን ይፈጠርበታል? ይህን መከላከል  ወንጀልን መከላከል ነው ነበር ያሉት፡፡

ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ እንዳይናድና እንዳይቀለበስ የሚያስችል ህግ እና ሥርዓት፣ ባህል፣ ልምድ አለን ተብሎ ነበር መወራት የነበረበት፡፡ እሳቸው በመታመማቸው ደግሞ ማዘንና ሀዘናችንን መግለጥ ነበረብን፡፡ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ እንዳይናድ እና የተናደ ሲስተሙ መቀጠል አለበት፡፡

ይህን ማረጋገጥ የሚችል ህግና ሥርዓት ደግሞ አለን፡፡ ከዚህ በመለስ ግን ህመማቸውና የት እንደተኙ ካልተነገረን የሚለው ጥያቄ ተገቢ አይደለም፣ ወንጀልም ነው፡፡ የሚል ዓይነት መልዕክት ያለው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

**ማጠቃለያ፣**

በመግቢያዬ የጠቀስኩት እና ለመጣጥፌ መነሻ የሆነኝ የሪፖርተሩ ተሚገት ፀሐፊ እንደገለጸው "ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደማንኛውም የአገር መሪ የሚወደሱበት እና የሚኮነኑባቸው በርካታ ፖሊሲዎች ይኖራሉ፡፡" በሚለው እስማማለሁ። በሀገራችን በምሥራቅ አፍሪካ ቀጠና የሠላም ሁኔታ፣ በዓለም አቀፍ የንግድ መስኮችና ህግጋቶች ላይ፣ በሀገራችን ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት፣ በተለይ የብሄር ብሄረሰቦችን የዘመናት ጥያቄ በመለስ (ፌዴራላዊ ሥርዓት በመገንባት)፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በአጠቃላይ፤ በተለይም በአፍሪካ ህብረት፣ በአባይ ተፋሰስ አገሮች የአካባቢው ኃያል መንግሥት በማድረግ፣ በአካባቢ ጥበቃ ኢትዮጵያን ታዋቂና ተሰሚነት እንዲኖራት አድርገዋል - ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡፡

"ሆኖም በየትኛውም ሰብዓዊ መስፈርት ለማንም ቢሆን ሞትን መመኘት አላግባብ ብቻ ሳይሆን የሞራል ዝቅጠትንም ያመለክታል፡፡ ተቃዋሚው ወገን ከተመኘው ግብ መድረስ ሲሳነው ከሞት ጋር ቅንጅት ለመፍጠር መሞከሩ አሁን በምንገኝበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን የፖለቲካ ባህላችን ምን ያህል ኋላ ቀር እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የተቃዋሚው ፖለቲካዊ ምህዳር ሁልጊዜ የሚያተኩረው ከመንግሥት በሚወጡ እለታዊ መግለጫዎች ወይም ውሣኔዎች ላይ እንጂ በዋና አገራዊ ፖሊሲዎች ላይ አይደለም፡፡"

በአገራችን ለተከታታይ ዓመታት የመጣውን የምጣኔ ሀብት እድገት ተቃዋሚዎችና ነፃ ነን የሚሉ አንዳንድ ጋዜጦች በጉዳዩ ላይ አትኩረው ከመተንተን ይልቅ በሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት ላይ ብቻ በመጣበቅ ዕድገቱንም ሆነ ውድቀቱን እየተከታተሉ ወቅታዊ መረጃ የሚሰጡትን እንደ ዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅትን ምስክርነት ሳይቀር እውቅና ሲነሱ መቆየታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ይህ የተሳሳተ መሠረታዊ ባህሪ በመሆኑ ምናልባት ሳይገርመን ቆይቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በሰው ህመም መፍረድና ማንጓጠጥ በእግዚአብሄር ሥራ ውስጥ እንደመግባት የሚቆጠር እና ይህ ደግሞ ከኃያሉና ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ከሆነ ገዥ ጋር መሳፈጥ አይሆንም ወይ? የሚል ጥያቄ እንዳነሳ ያስገድደኛል፡፡

የብዙኃኑ ህዝብ ፍላጎት ልማትና ፈጣን እድገት ማምጣት ነው፡፡ ህዝቡ ራዕይ በሌላቸው ተቃዋሚዎችና ፕሬሶች ምክንያት ሀገር ስትታመስ ማየት አይፈልግም፡፡ አገራችን በዓይን በሚታይ የእድገት ጎዳና ላይ ሆና የኋሊት እየተጓዘች ነው የሚሉት የሀገሬ ተቃዋሚዎችና አንዳንድ ፕሬሶች፤ አገር ሠላም ውላ ሠላም እያደረች አገር በጦርነት እየታመሰች ነው ሲሉም ሳያፍሩ ይጨምሩልናል፡፡

አዳዲስ የልማት አቅጣጫዎች ሲዘረጉ ህዝብ ተፈናቀለ፤ አገር ተበላሸ ሲሉ ነጋሪት ይጎስማሉ፡፡ ዛሬ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መጠነኛ ህመም አጋጥሟቸዋል ሲባል ድንኳናቸውን ጥለው ጥሩንባቸውን ይነፋሉ፤ ያሚርታሉም፡፡